# ዳግማዊ ዓይኑ ይጥፋ

በደሳለኝ በርሄ- መልሥ ለገጣሚ ዳግማዊ ዳዊት



ነውጠኛ ነፍጠኛ ዳግማዊ ዓለመኛ

ነፍሰ ገዳይ ጨካኝ ዘራፊ ቀማኛ

ደግሞ “ፍችው” ይላል ይፈታና ቤቱ

የትናንት ጭካኔው የዛሬም ድፍረቱ።

ትናንት ብቻ በላ ዛሬም ቅሚያ አማረው

ይህ ዳግማዊ ዳዊት ፍጥረቱ ከምን ነው?

ከሲያል አምልጠ ከሳጥናኤል መንደር

ወይስ ከናዚ ካምፕ ከሂትለር ሰፈር

መልካሙን የማያይ ከጥፋቱ በቀር።

እንዴ "ጨክ በል" ይላል ጨሆ ይለፍፋል

"ፍችውና ላግባሽ" ይላል ከጥሩ ባል

"ዛሬን አልኖርኩትም" እያለ ያለቅሳል።

እርሱ ለሴስነ መጨህ ስላማረው

መንግስት የሚናጋ ምነው የመሰለው?

ይመኛታል እንጅ በህልም ይቃዣታል

ቆንጆዋን እመቤት በየት ያገኛታል?

አይኖራትም ዛሬን ልክ እንደትናንቱ

የነፍጠኛ ሥርዓት አክትሟል የጥንቱ።

ማንስ ከለከለው በሰላም ለመኖር

አልማር አለ እንጅ ከአባሻወል ሰፈር

ማየት ነው ሚስጥሩን የኃይሉን ግንባታ

የትም አያደርስም የእናንተ ጋጋታ

ጥፋት ነህ ዳግማዊ የማታ የማታ።

አገር እንድትለማ እውቀት እንዲስፋፋ

ዘላቂ እንዲሆንም የሕዝባችን ተስፋ

ደግ የማይታየው ያ ቀቢፀ-ተስፋ

ማየት የተሳነው መልካሙ ሲፋፋ

ይህ ዳግማዊ ዳዊት ሁለት ዓይኑ ይጥፋ።

ደሳለኝ በርሄ፡ desberhe@gmail.com